# የቤተሰብ አባላትን ወደደቡብ አፍሪካ ለማስመጣትና ለመቀላቀል በኦንላይን የማመለክተው እንዴት ነው?

ይህ ሰዎች በደቡብ አፍሪካ ያለውን የጥገኝነት አሠራር ሥርዓት እንዲረዱ የሚያግዝ ሰነድ ነው። እባክዎን ይህ መመሪያ ብቻ እንጂ በሕግ የተደነገ ምክር አለመሆኑን ይገንዘቡ። ይህ መረጃ ሊቀየር ስለሚችል ራስዎን በመረጃ ለማዘመን ይህን ድረ-ገጽ ይመልከቱ: www.scalabrini.org.za/informationabout-asylum-in-south-africa።

በዚህ ሰነድ ላይ ተመስርተው ለሚወሰዱ እርምጃዎች በኬፕታውን የሚገኘው የስካሊብሪኒ ማዕከል ኃላፊነቱን አይወስድም።

## ደረጃ ፩፡



**የግልዎ ኢሜይል አካውንት እንዳለዎት እርግጠኛ ይሁኑ**

## ደረጃ ፪፡



**ለትክክለኛውና ለመረጡት የጥገኝነት ጥያቄ መቀበያ ቢሮ *(REFUGEE REECEPTION OFFICE)* ኢሜይል ይላኩ**

## ደረጃ ፫፡



**ለላኩት ኢሜይል መልስ እስኪሰጥዎ ይጠብቁ። የቀጠሮ ደብዳቤ ይላክልዎታል**

## ደረጃ፬፡



**በቀጠርዎ መሰረት በመረጡት የጥገኝነት ጥያቄ መቀበያ ቢሮ *(REFUGEE RECEPTION OFFICE)* በአካል ይገኙ**

ዝርዝር መረጃዎችን በቀጣይ ገጾች ይመልከቱ

Scalabrini
Centre of Cape Town

## ደረጃ ፩፤ የግልዎ ኢሜይል አካውንት እንዳለዎት እርግጠኛ ይሁኑ

የቤተሰብ ጉዳይ ማመልከቻ ሂደትዎን ለመጀመር የግል ኢሜይል አካውንት መኖር በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ነው። የግል ኢሜይል አካውንት ከሌልዎ ማውጣት ግዴታዎ ነው። በኢንተርኔት ካፌዎች ውስጥ ያሉ ኢሜይል አካውንቶችን እንዲሁም ከሌሎች ጋር የሚጋሯቸውን ኢሜይል አካውንቶች አይጠቀሙ፤ ለዚህ ሂደት የሚጠቀሙት የግልዎ ኢሜይል አካውንት መሆን አለበት። ይህን አካውንት ወደፊት ስለሚጠቀሙበት፣ የመግቢያ ዝርዝር (log in details) እና የይለፍ ቃላቶች (password) ሊያስታውሷቸው የሚችሉ መሆናቸውን ያረጋግጡ። በአሁኑ ወቅት የሀገር ውስጥ ጉዳዮች መሥሪያቤት (Department of Home Affairs) አብዛኞቹ አገልግሎቶች የሚሰጡት በኦንላይን ነው። ከሀገር ውስጥ ጉዳዮች መሥሪያቤት (Department of Home Affairs) ጋር ግንኙነት ለማድረግ ከላይ የተጠቀሰውን የግል ኢሜይል አካውንትዎን እንዲጠቀሙ እንመክራለን።

## ደረጃ ፪፤ ለትክክለኛውና ለመረጡት የጥገኝነት ጥያቄ መቀበያ ቢሮ *(REFUGEE REECEPTION OFFICE)* ኢሜይል ይላኩ

«የቤተሰብ ቅልቅል» ("family joining") የማመልከቻ ሂደትን የሚጀምሩት ኢሜይል በመላክ ነው። ሆኖም በሂደቱ የኋለኛ ምዕራፍ ላይ በሚሰጥዎ ቀጠሮ መሰረት ወደሚመለከተው የጥገኝነት ጥያቄ መቀበያ ቢሮ (Refugee Reception Office) በመሄድ በአካል መገኘት ይኖርብዎታል። የሚልኩት ኢሜይል ለመጨረሻ ጊዜ የስደተኝነት ሰነድዎን ወይም ወረቀትዎን ያደሱበት ወይም ያራዘሙበት የጥገኝነት ጥያቄ ማቀበያ ቢሮ (Refugee Reception Office) መሆኑን እርግጠኛ ይሁኑ። ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ውስጥ ትክክለኛውን የኢሜይል አድራሻ ይምረጡ።

| | |
|---|---|
| ኬፕታውን፤ **CAPE TOWN REFUGEE RECEPTION OFFICE:** | inquiries.ctrro@dha.gov.za |
| ፕሪቶሪያ፤ **PRETORIA (DESMOND TUTU) REFUGEE RECEPTION OFFICE:** | inquiries.dtrro@dha.gov.za |
| መሲና፤ **MUSINA REFUGEE RECEPTION OFFICE:** | inquiries.musinarro@dha.gov.za |
| ደርባን፤ **DURBAN REFUGEE RECEPTION OFFICE:** | inquiries.durbanrro@dha.gov.za |
| ሔበርሃ፤ **GQEBERHA REFUGEE RECEPTION OFFICE (FORMERLY PORT ELIZABETH):** | inquiries.perro@dha.gov.za |

**ለሀገር ውስጥ ጉዳዮች መሥሪያቤት** (Department of Home Affairs) **በምትልኩት ኢሜይል ውስጥ** “Subject” **በሚለው ሳጥን ውስጥ** “Family Joining” **ብላችሁ ከጻፋችሁ በኋላ ስማችሁንና የፈቃድ ወረቀታችሁን ቁጥር** (**የፋይላችሁን ቁጥር**) **አስከትሉ። በታችኛው የኢሜይል ሰሌዳ ላይ በምትጽፉት የኢሜይል መልእክት ውስጥ የሚቀላቀላችሁን የቤተሰብ አባል በመጥቀስ በዚህ መልኩ መጻፍ ትችላላችሁ፤** "Dear Sir or Madam, I am kindly requesting family joining for my husband / wife / children / elderly parent." **ከዚያ በመቀጠል ሙሉ ስማችሁን እና የፈቃድ ወረቀት ቁጥራችሁን እንዲሁም የተንቀሳቃሽ ስልክ ቁጥራችሁን ከስር ጻፉ። ከላይ ስማችሁንና የፈቃድ ወረቀታችሁን ቁጥር** (**የፋይላችሁን ቁጥር**) **ጽፈናል በሚል በድጋሚ መጻፍ እንዳትረሱ። ከዚያ ኢሜይሉን ይላኩት።**

## ደረጃ ፫፤ የቀጠሮ ደብዳቤ እስኪላክልዎት ይጠብቁ። በቀጠሮው መሰረት ወደቦታው ይሂዱ

**ለሀገር ውስጥ ጉዳዮች መሥሪያቤት** (Department of Home Affairs) **ኢሜይል ከላኩ በኋላ የቀጠሮ ደብዳቤ የያዘ ኢሜይል መልሰው ይልኩልዎታል። ደብዳቤው ከመልስ ኢሜይሉ ጋር የሚያያዝ ሲሆን ወደሚመለከተው የጥገኝነት ጥያቄ መቀበያ ቢሮ** (Refugee Reception Office) **መቼ መሄድ እንዳለብዎትም ይገልጻል።**

- **በቀጠሮው መሰረት ወደሚመለከተው የጥገኝነት ጥያቄ መቀበያ ቢሮ** (Refugee Reception Office) **መሄድዎን ልብ ይበሉ።**
- **ሊቀላቀልዎ የሚፈልጉትን የቤተሰብ አባላት ይዘው ይሂዱ። እነዚህ ሰዎች የትዳር አጋር** (**ባል ወይም ሚስት**)**፣ አዛውንት ወላጆች፣ ወይም ልጆች ሊሆኑ ይችላሉ።**
- **ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ማንኛቸውም አስፈላጊ ሰነዶችን ይዘው ይሂዱ። እነዚህ ሰነዶች የጋብቻ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት** (**ሰርተፊኬት**)**፣ የልደት ምስክር ወረቀት** (**ሰርተፊኬት**)**፣ ወይም እነዚህ ሰዎች ቤተሰብ መሆናቸውን የሚያሳዩ ማንኛቸውም ሰነዶች ሊሆኑ ይችላሉ።**

